# ሞጁል 3

## የአሰልጣኙ መምሪያ

### የምብዛት ተልእኮ ትምህርት

ጤናማ ቤተክርስቲያናትን መትከል

multiplication network

*more churches, stronger churches*

ትርጉም፤ ሚልክያስ ለዕላጎ ሸምሱ - 2012

## የብዜት ተልዕኮ
## የቤተክርስቲያን ተከላ ስርአተ ትምህርት ዳሰሳ

| | ሞጁል 1<br>ጤናማ የቤተክርስቲያን ተከላ | ሞጁል 2<br>መልካምን የምስራች ለመናገር መዘጋጀት | ሞጁል 3<br>የእግዚአብሔርን ዕ ቅድ መረዳት | ሞጁል 4<br>መልካሙን ዜና ላሰሙ ማድረስ | ሞጁል 5<br>ሰዎችን ወደ እምነት ማንቀሳቀስ | ሞጁል 6<br>ደቀመዛሙርትን ማሳደግ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማጥኛዎች | የጤናማ ቤተክርስቲያናት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረቶች | የጤናማ ቤተክርስቲያናት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረቶች | የጤናማ ቤተክርስቲያን ተልዕኮአዊ መሰረቶች | የጤናማ ቤተክርስቲያናት ስልታዊ መሰረቶች | ወንጌሉን መኖር | ክርስቲያናዊ እድገት: ክርስቶስ ዕይታችን ማዕከል (ክርስቶስን ማዕከል ማድረግ) |
| ክፍለትምህርት 1 | ጤናማ ቤተክርስቲያን ምንድን ነው? | መንፈሳዊ ካርታ: የትናት መርሆዎች | እግዚአብሔር ያሳየኝ: የጥናት ውጤትህን ማቅረብ | በእምነት መጽደቅ | የወንጌል እንቅፋት | ታላቁ ተልዕኮ እና ቤተክርስቲያን ተከላ |
| የጤናማ ቤተክርስቲያን ጽንሰ አሳብ | ጥርት ያለ ራዕይን ማስተዋወቅ | ተልዕኮ፣ አውድ፣ እና አውዳዊነት | ራዕይ፣ አውድ፣ እና አውዳዊነት | በእግዚአብሔር መጠራትን ማጽናት | ወንጌል | ወንጌል እና ደቀመዝሙር |
| ክፍለትምህርት 2 | ጤናማ የቤተክርስቲያ ተከላ አገልጋይ ምንድን ነው? | ኢየሱስ ይህን አድርጎልኛል! የግል ምስክርነታችሁን ማደርጀት እና ማካፈል | እግዚአብሔር ያሳየኝ: ምስክርነትህን ማካፈልና የጉዞ ጸሎት | የመሪነት መጽሀፍ ቅዱሳዊ መርሆዎች | የለውጥ ሂደት 1 | የደቀመዝሙርነት ትምህርትን የተሳካ ለማድረግ የሚረዱ መንገዶች |
| የጤናማ ቤተክርስቲያን ጽንሰ አሳብ | መጠራቱ በእግዚአብሔር የተረጋገጠ | ወንጌል | ራዕይ፣ አውድ እና አውዳዊነት | መሪዎችን ማስታጠቅ | ወንጌል | Discipleship |
| ክፍለትምህርት 3 | "የመጨረሻ" አስተሳሰብ: እግዚአብሔር ምን ይፈልጋል? | ትናንሽ ቡድኖችን መምራት | የቤተክርስቲያን ተከላ መሪ ዕቅዱ: የእግዚአብሔርን ራዕይ በመንፈስ መረዳት | ወንጌል ስርጭት እና የቤተክርስቲያን ተከላ | የለውጥ ሂደት 2 | Know Your Goal, Know Your People |
| የጤናማ ቤተክርስቲያን ጽንሰ አሳብ | ጥርት ያለ ራዕይን ማስተዋወቅ | ወንጌል፣ ደቀመዝሙር እና መሪዎችን ማስታጠቅ | ጥርት ያለ ራዕይን ማስተዋወቅ | ወንጌል | ወንጌል | ደቀመዝሙር |
| ክፍለትምህርት 4 | የቤተክርስቲያ ተከላ ዙር | ከመጽሐፉ አሳብመውሰድ 2: የእግዚአብሔርን ቃል መመልከት | የቤተክርስቲያን ተከላ መሪ ዕቅዱ: ተልዕኮን መተርጎም | የጥናት ቡድን መመስረት | በቡድን ወንጌልን ማሰራጨት | ከመጽሐፉ አሳብመውሰድ 2: የእግዚአብሔርን ቃል ካለንበት ሁኔታ ጋር ማዛመድ |
| የጤናማ ቤተክርስቲያን ጽንሰ አሳብ | ጥርት ያለ ራዕይን ማስተዋወቅ | ወንጌል እና ደቀመዝሙር | ጥርት ያለ ራዕይን ማስተዋወቅ | ወንጌል እና | ወንጌል | ወንጌል እና ደቀመዝሙር |
| ክፍለትምህርት 5 | አነስተኛ ቡድን ለምን አስፈለገ? | ለቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎትህ የጸሎት ቡድን ማንቀሳቀስ | የቤተክርስቲያን ተከላ መሪ ዕቅዱ: እሴትን መተርጎም | ወንጌል እና የማህበረሰቡን አስፈልጎት መድረስ | ልምምድ: የቡድን ልምምድ | ንጽረተ ዓለማትን መረዳት |
| የጤናማ ቤተክርስቲያን ጽንሰ አሳብ | ወንጌል እና ደቀመዝሙር | ወንጌል | ጥርት ያለ ራዕይን ማስተዋወቅ | ግልጋሎት | ወንጌል | በእግዚአብሔር መጠራትን ማጽናት |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ክፍለትምህርት 6 | ከመጽሀፉ አሳብመውሰድ I: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲናገረን መፍቀድ | የጸሎት ኮንሰርት: መዝ 95 | የቤተክርስቲያን ተከላ መሪ ዕቅዱ: ስልትን መተርጎም | ከመጽሀፉ አሳብመውሰድ 3: የእግዚአብሔርን ቃል መተርጎም | መሪ ዕቅድን ማቅረብ | የጸሎት ኮንሰርት እግዚአብሔርን ስለታማኝነቱ ማመስገን |
| የጤናማ ቤተክርስቲያን ጽንሰ አሳብ | ወንጌል እና ደቀመዝሙር | አምልኮ | ጥርት ያለ ራዕይን ማስተዋወቅ | ወንጌል እና ደቀመዝሙር | የጽንሰ አሳብ ውህደት | አምልኮ |
| | **ሞጁል 7 ቡድን መገንባት** | **ሞጁል 8 ቡድን መገንባት** | **ሞጁል 9 ሰዎችን መንከባከብ** | **ሞጁል 10 ቤተክርስቲያንን መመስረት** | **ሞጁል 11 ለወደፊት ማቀድ** | **ሞጁል 12 በአንድነት ወደፊት መንቀሳቀስ** |
| ማጥኛዎች | በወንጌል የተለወጠ | ለትሁታን ጸጋን ይሰጣል | ፍቅር፤ የአገልግሎት መሰረት | ዓለምን ያምን ዘንድ: ዮሐ 17 | ዋጋን መተመን | ዓለም ሁሉ እስኪሰማ! |
| ክፍለትምህርት 1 | የቤተክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረቶች | የቡድን ስራ: ከሌሎች ጋር ውጤታማ በሆነ መልኩ መስራት | በአብሮነት ውስጥ የሚደረግ የወንጌል ስርጭት | የቤተክርስቲያን ጥምር ተግባራት | የባለአደራነት ትምህርትን መተዋወቅ | ግጭትን መፍታት |
| የጤናማ ቤተክርስቲያን ጽንሰ አሳብ | የጽንሰ አሳብ ውህደት | መሪዎችን ማስታጠቅ | ወንጌል | የጽንሰ አሳብ ውህደት | የግብአት ባለአደራ | ህብረት |
| ክፍለትምህርት 2 | ቤተክርስቲያን: A Living Organism | ቡድን ማደርጀት | የቡድን አባላትን መንከባከብ | በጸጋ ስጦታዎች ማገልገል | የገንዘብ ባለአደራ | ንስሃ እንደ የሕይወት ዘይቤ |
| የጤናማ ቤተክርስቲያን ጽንሰ አሳብ | የጽንሰ አሳብ ውህደት | ቡድን ማደርጀት | ህብረት | የጸጋ ስጦታው ተለይቶ የሚሰማራ የክርስቶስ አካል | የንብረት ባለአደራ | ህብረት |
| ክፍለትምህርት 3 | መቼ ነው አንድ ቡድን ቤተክርስቲያን የሚባለው? | የቡድን ውይይት ሂደት | ማህበረሰባችንን መንከባከብ | የጸጋ ስጦተ መለያ ቅጹን መጠቀም እንዴት ይቻላል | የስልታዊ ዕቅድ ሰርቶ ማሳያ | ተቃውሞ እና ተሃድሶ: የቤተክርስቲያን ስርአት |
| የጤናማ ቤተክርስቲያን ጽንሰ አሳብ | የጽንሰ አሳብ ውህደት | ደቀመዝሙር | ወንጌል፣ አውድ እና አውዳዊነት | የጸጋ ስጦታው ተለይቶ የሚሰማራ የክርስቶስ አካል | | ህብረት |
| ክፍለትምህርት 4 | ከመጽሀፉ አሳብመውሰድ 4: ከመጽሐፉ አሳብ የመውድ ጥናት መንገዶች | አዳዲስ የቡድን መሪዎችን ማሰልጠን | የሚያድግ ቤተክርስቲያን መገለጫዎች | የመንፈሳዊ ውጊያ ሂደት | | ሌሎችን ለአገልግሎት ማሰማራት |
| የጤናማ ቤተክርስቲያን ጽንሰ አሳብ | ደቀመዝሙር | ደቀመዝሙር ማድረግ እና መሪዎችን ማስታጠቅ | የጽንሰ አሳብ ውህደት | ህብረት | | መሪዎችን ማስታጠቅ |
| ክፍለትምህርት 5 | የክርስቲያን መሪ ፕሮፋይል | የተግባቦት ዘይቤ | አገልጋይ መሪነት | ቤተክርስቲያንን ወደ አምልኮ መምራት | | ትልቁ የክርስቶስ አካ፣ ቤተክርስቲያናችን እና ማህበረሰብ |
| የጤናማ ቤተክርስቲያን ጽንሰ አሳብ | መሪዎችን ማስታጠቅ | መሪዎችን ማስታጠቅ | መሪዎችን ማስታጠቅ | አምልኮ | | ህብረት |
| ክፍለትምህርት 6 | መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስብከት 1: መልዕክቱን መረዳት | መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስብከት 2: አድማጭን መረዳት | የጸሎት ኮንሰርት: ኤፌ 3-5 | መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስብከት 3: ሰባኪው እንደ ግለሰብ | | የጸሎት ኮንሰርት: ወንጌልን ለማሰራጨት መጸለይ |
| የጤናማ ቤተክርስቲያን ጽንሰ አሳብ | አምልኮ | አምልኮ | ህብረት | ህብረት | የግብአት ባለአደራ፤ ጥርት ያለ ራዕይን ማስተዋወቅ | ወንጌል |
| | | | | | | |

# የማብዛት ተልዕኮ

**ጤናማ ቤተክርስቲያን ተከላ ሞጁል**

**መልቲፕሊኬሽን ኔትዎርክ ሚኒስተሪስ**

**ብዙ አጥቢያ ያላት/ ጠንካራ ቤተክርስቲያን**

2007 ዓ.ም

ይህ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዮች ማሰልጠኛ ማኑዋል በAbridged Omega Course እና Multiplication Network Ministries’ ጤናማ ቤተክርስቲያን መትከል የተሰኘ የማስተማሪያ መጽሐፍትን በማዋሃድ የተዘጋጀ ነው፡፡

MNM ከ Training Center for Church Planters እና ከ World Ministries ባገኘው ፈቃድ መሰረት ይህን ማስተማሪያ ለቤተክርስቲያን ጥቅም እንዲህ አቅርቦታል፡፡

እናንተም ይህን ማስተማሪያ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መጠበቂያዎች እስከተከተላችሁ ድረስ ይህን መጽሐፍ እንድታባዙና እንድታሰራጩ ማበረታቻችን የሰጠናችሁ ፈቃድ ይሁንልን፡፡

1. ለመጽሐፉ ጸሐፊያን እና ተርጓሚያን ዕውቅና መስጠት
2. መጽሐፉ ላይ ማሻሻያ አድርጋችሁ እንደሆን እርሱን ማሳወቅ
3. ለማሳተሚያ ካወጣችሁት ዋጋ በላይ አለማስከፈል እና
4. ከ አንድ ሺህ ኮፒ በላይ አለማሳተም

ኦሜጋ ኮርስ፡-

ተግባራዊ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት ማስተማሪያ

| | ለአንድ ቀን ስልጠና የጊዜ ደዘት እንደ ምሳሌ የቀረበ | |
|---|---|---|
| | የሞጁል አንድ መግቢያ 3 | 2:00 |
| | የጤናማ ቤተክርስቲየን<br>ተልዕኮአዊ መሰረቶች | 2:15 |
| | ሪፖርት ማቅረብ | 2:30 |
| ክፍለ ትምህርት<br>አንድ | እግዚአብሔር ያሳየኝ:<br>የጥናት ውጤትህን ማቅረብ | 3:00 |
| | ረፍት | 4:00 |
| ክፍለ ትምህርት<br>ሁለት | እግዚአብሔር ያሳየኝ:<br>ምስክርነትህን ማካፈልና የጉዞ ጸሎት | 4:15 |
| ክፍለ ትምህርት<br>ሶስት | ራዕይ፣ አውድ እና አውዳዊነት | 5:15 |
| | የምሳ ረፍት | 6:15 |
| ክፍለ ትምህርት<br>አራት | የቤተክርስቲያን ተከላ መሬ ዕቅዱ: የእግዚአብሔርን ራዕይ<br>በመንፈስ መረዳት | 7:15 |
| ክፍለ ትምህርት<br>አምስት | የቤተክርስቲያን ተከላ መሬ ዕቅዱ:<br>እሴትን መተርጎም | 8:15 |
| | የሻይ ረፍት | 3:15 |
| ክፍለ ትምህርት<br>ስድስት | የቤተክርስቲያን ተከላ መሬ ዕቅዱ:<br>ስልትን መተርጎም | 9:30 |
| | መዝጊያ | 10:30 |
| | የቀኑ ጥናት ፍጻሜ | 10:45 |

# የእግዚአብሔርን ራዕይ መረዳት

## ሞጁል 3

**የትምህርቱ ዓላማ፡-**

- ከዚህ ስልጠና በኋላ ተሳታፊዎች በሚከተሉት አሳቦች ተግባር እና በመካከላቸው ያለውን ልዩነት በራሳቸው አገላለጽ ማስቀመጥ ይችላሉ፡- (1) ራዕይን የሚገልጥ አርፍተነገር (2) ተልእኮን የሚገልጥ አርፍተነገር (3) እሴቶችን የሚገልጥ አርፍተነገር (4) ቤተክርስቲያን ለመትከል የተነደፈ ስልት፡፡
- ተሳታፊዎች አዲስ ሊተክሉት ላሰቡት ቤተክርስቲያን ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴት እና ቤተክርስቲያን የምትከተለው ስልትን የሚያሳይ አርፍተነገር መጻፍን ያዳብራሉ፡፡
- "ለሞጁል 4 የሚዘጋጀውን የተግበራ እቅድ" በመጠቀም ተሳታፊዎች ስለራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴት እና ስልት ከመጋቢያቸው፣ ከሚደግፏቸው የቤተክርስቲያን መሪዎች እና ሌሎች በዚህ አገልግሎት በሚሳተፉ ሰዎች (እንደየአስፈላጊነቱ) ጋር በመሆን የተማረትን በማካፈል ትምህርቱን የበለጠ ሊያጠነክረት ይችላሉ፡፡

**ለአሰልጣኙ የተሰጠ ማስታወሻ፡-** በዚህ ሞጁል "ክፍለትምህርት 5፡- የቤተክርስቲያን ተከላ እቅዱ፡- እሴቶች" ለሚለው ክፍል የተቀመጠለት ጊዜ አንድ ሰዓት ነው፤ ይሁን እንጂ ክፍሉ የሚፈልገው 30 ደቂቃ ብቻ ነው፡፡ የዚህ ክፍል አብዛኛው ስራ የሚያልቀው በሞጁል 4 የቤተክረስቲያን ተከላ አገልጋዩ የትግበራ እቅድ በሚለው ክፍል ነው፡፡ እንደየአስፈላጊነቱ ተጨማሪ ጊዜ መውሰድ ትችላላችሁ፤ ለምሳሌ፡- ከዚህ ቀደም የነበረውን ትምህርት ለመከለስ፣ ለማስተማር፣ በትናንሽ ቡድን ሆኖ ለመጸለይ፣ ተሳታፊዎች ያላቸውን ጥያቄ እና የገጠማቸውን ተግዳሮት ለመፍታት ወይንም ቀደም ብሎ ከዚህ ትምህርት መሰናበት ያለባቸውን ማወቅ ይህን ትርፍ ጊዜ መጠቀም ይቻላል፡፡

**ለሞጁል 3 የሚሆን መግቢያ**

**አሰልጣኙ መግቢያውን የሚያስተዋውቅበት ነጥብ (2 ደቂቃ)**

- ተሳታፊወችን ሞቅ ባለ፣ ፍቅር በተሞላ እና በሚያነቃቃ ሁኔታ የእንኳን ደህና መጣችሁ መልእክትህን አቅርብ
- ከዚያም በጸሎት የቀኑን ትምህርት ለእግዚአብሔር ክብር ሆን ዘንድ አሳልፈህ ስጥ

**ዝምታን ለመስበር የሚከወን ተግባር (5 ደቂቃ)**

እያንዳንዱ ሰው በቡድን ውስጥ ተሳታፊ ስለሆነ ሌላ ሰው የሚሆን ጥያቄ እንዲያስብ የተወሰኑ ደቂቃዎችን መስጠት፤ ከዚያም ቡድኑን መሪው በሚፈልገው መንገድ በማሰባጠር በአሳባቸው ያዘጋጁትን ጥያቄዎች ለደረሳቸው ሰው በማቅረብ የመሳሹን መልስ እና ስም እንዲጽፉ አድርግ፡፡ አስር ደቂቃ የሚሆን ጊዜ ለመጠያየቅ ከወሰዱ በኋላ ቡድኑን በጋራ በመሰብሰብ እያንዳንዱ ሰው ከጠየቀው ጥያቄ ስለግለሰቡ ያወቀውን እንዲናገር እድል ስጥ፡፡ ጥሩ ጥያቄዎች በፈጠርን ቁጥር አስገራሚ መልሶች እና ገኛለን፡፡

ራእይ፣ ተልእኮ፣ እሴት እና ስለትን ለማስተዋወቅ የሚሆን መግቢያ (8 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-**

- የሚከተሉትን ቃላት በጥቁር ሰሌዳ፣ ነጭ ሰሌዳ፣ ወይንም በወረቀት ላይ ጽፈህ ክፍል ውስጥ ለጥፍ፤ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴት እና ስልት
- ተሳታፊዎችን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጠይቅ፡-
    1. እንዚህን ጽንሰ አሳቦች እንዴት ትረዳቸዋለህ?
    2. አንዳቸው ከሌላቸው በምን ይለያሉ?
    3. ራእይ፣ ተልዕኮ፣ እሴት እና ስልት ለቤተክርስቲያን ተከላ ምን አይነት ጥቅም ይሰጣሉ?

- እንዲህ በል "ዛሬ ስለሩስ፣ ተልእኮ፣ እሴት እና ስልት ለቤተክርስቲያ ተከላ የሚሰጡትን ጥቅም እንመለከታለን። እነዚህ ጽንሰ ሐሳቦች ቤተክርስቲያ ማ እንደሆነች እና ምን እየሰራች እንዳለች ደግሞም ወደፊት ምን እንደምትሰራ በተጨባጭ የምታስረዳበት መንገድ ነው። በአጭሩ እነዚህ ጽንሰ ሐሳቦች የቤተክርስቲያንን ባህሪ እና ስራ ገለጭ ናቸው። ቤተክርስቲያን በምንተክልበት ወቅት ጥቅም ላይ የምናውለው አንድ መርህ ተልዕኮአዊ (ከተልዕኮ ጋር የተገናኘ) ሆኖ፤ ስለሩዕዩ፣ ተልዕኮ፣ እሴት እና ስለት የምናደርገው ሐሳሳ መሰረቱን የሚያደርገውም ተልዕኮን መሰረት ያደረገ ጤናማ ቤተክርስቲያን መትከልን ነው።"

# ተልእኮአዊ መሰረት

# ስጤናማ ቤተክርስቲያናት (15 ደቂቃ)

### የመክፈቻ ተግባር (2 ደቂቃ)

የአሰልጣኙ መምሪያ:- ተሳታፊዎች ቤተክርስቲያን የሚተክሉበትን ምክንያት እንዲናገሩ ጠይቅ፤ ከዚያም ከሚመስሉት መልሶች በዚህ ክፍለትምህርት የተጠቀሱት የትኞቹ መልሶች እንደሆን እንዲለዩ እርዳ ስጥ።

### የጥሞና መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት (13 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ:-** አንድ ፈቃደኛ ተሳታፊ ስለቤተክርስቲያን ተልእኮ የሚያትተውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በጠቀሳሳ ለተሳታፊዎች እንዲያነብብ እርዳ ስጥ። ከዚያም ተሳታፊዎች ከዚህ በታች የተሰጡትን ጥያቄዎች በሚማሩበት ወቅት፤ በመማሪያ መጽሐፋቸው ያለውን ክፍት ቦታ እየሞሉ እንዲከታተሉ አድርግ።

**መርህ 1** ቤተክርስቲያን <u>ምንድን ናት</u> (<u>አስፈላጊነቷ/ባህርይዋ</u>)።

**አንብብ:-** 1ጴጥ 2:9-12፤ ኤፌ 4:24፤ 1ቆሮ 12:12-13

**የአሰልጣኙ መምሪያ:-** ከእነዚህ ክፍሎች ተሳታፊዎች ስለቤተክርስቲያን/የእግዚአብሔር ህዝብ ምን እንደተማሩ ጠይቅ።

እንዲህ በል "ቤተክርስቲያኒቱ፤ የእርሱ ህዝብ እንዲሆኑ የተመረጡ፣ በእግዚአብሔር የተፈጠሩ ማህበረሰቦች ሲሆኑ ህዝብን እና ፍጥረትን ለመለወጥ መንገድ ሚሆኑ ናቸው።"

ቤተክርስቲያን በእውነተኛ ጽድቅና ቅድስና እግዚአብሔርን ለመምሰል በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠረ ማህበረሰብ ነው፡፡ ቤተክርስቲያን አንድ ቤተሰብ ስመሆን በመንፈስ ቅዱስ የተጋጠመ የክርስቶስ አካል ነው፡፡

**መርህ 2** ቤተክርስቲያ ምን ትከውናለች (ተግባሯ/አላማዋ)፡፡

**ዕንብብ፡-** ሐዋ 6፡1-7፤ ሐዋ 11፡19-26 እና ሐዋ 12፡25

የአሰልጣኙ መምሪያ፡- እንዲህ ብለህ ጠይቅ "በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ ቤተክርስቲያን ምን ትከውን ነበር?"

እንዲህ በል "ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ፣ ወንጌልን በተለየ አውድ በመቅረጽ እና በመስኮት ተልዕኮ ውስጥ አብሮ ሰራተኛ በመሆን የተገለጠውን የእግዚአብሔርን መንግስት ትሰብካለች/ታውጃለች፡፡ የክርስቲያን መቀደስ ከተቀመጠለት ወንጌሉን የማወጅ፣ ሌሎችን የመጥቀም እና አገልጋይነት ተግባር ጋር ተያያይዞ የሚከናወን ነው፡፡ ቤተክርስቲያ የምትሰራው የሆነችውን ነው፡፡ ልክ ውሻ የሚጮኸው በተፈጥሮው እንደዚያ ለመጮኽ የተሰራ እደሆነ ሁሉ፤ ቤተክርስቲያንም ተልዕኮዋን(ሌሎች በወንጌል የመድረስ ስራ) የምታከናውነው እንደዚሁ ተፈጥሮዋ ስለሆነ ነው፡፡"

**መርህ 3** ቤተክርስቲያን የምታደራጀው የምትከውነውን ነው(ቅርጽ/አደረጃጀቷ)፡፡

**ዕንብብ** ሐዋ 6፡1-4

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** ሐዋርያት እንዴት ቤተክርስቲያንን ማደራጀት እንደወሰኑ እንዲያብራሩ ተሳታፊዎችን ጠይቅ፡፡

**እንዲህ በል** "ቤተክርስቲያን የተሰጣትን ተልእኮ ለመወጣት እንዲያግዛት ለምትተገብረው ተግባር ቅርጽ ትሰጣለች፤ ይህም ተግባር በመንፈስ ቅዱስ፣ በቤተክርስቲያን እቅድ፣ ትግበራ፣ ምዘና እና ለውጥ እየተመራ ተልዕኮውን ተከትሎ ይጓዛል፡፡ በዚህ ክፍል ቁልፉ ሐሳብ ቤተክርስቲያን

ተፈትሮዋን እና ዓላማዋን በሚገባ ስታውቅ የተሰጣትን ተልዕኮ ለመፈጸም በሚረዳ መልኩ ቅርጽእና አደረጃጀቷን ታስተካክላለች፡፡"

## ሪፖርት ማቅረብ (30 ደቂቃ)

የአሰልጣኙ መምሪያ፡-

- የሪፖርት ማቅረቢያውን ቅጽ በመጠቀም ተሳታፊዎች ከሞጁል 2 ማብቂያጀምሮ እስከዚህ ጊዜ  ያላቸውን ቤተክርስቲያን ተከላ ተግባራት እንዲያቀርቡ እድል ስጥ፡፡
- በዚህ ረገድ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡትን አመስግን፤ በዚህ ጉዳይ ተስፋ ወደመቁረጥ የቀረቡትን ደግሞ አበረታታ፡፡ ጊዜ የምታገኝ ከሆነ ጠቅላላውን ተሳታፊ፤ በትንንሽ ቡድኖች በመክፈል የቤተክርስቲያን ተከላን በተመለከተ አንደችሁ ሊላችሁ ጸልዩ፡፡
- ሪፖርት የሚደረግበትን ሂደት በተመለከተ የሚነሱ ማንኛውም ሌነት ጥያቀዎችን መልስ፡፡

# የቤተክርስቲያን ተከላ ሪፖርት

ወርሃዊ ሪፖርት

## ጠቅላላ መረጃ

| ሪፖርቱ የተደረገበት ወር | | የምክርና ድጋፍ አገልግሎቱ ተከናውኗል | አዎን | የለም |
|---|---|---|---|---|

| | |
|---|---|
| የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ ስም | |
| ቤተክርስቲያኒቱን የሚተክለው ሰው አካባቢ | |
| የአካባቢው አስተባባሪ | |

| ግለሰቦች | ወርሃዊ ግብ | ወርሃዊ ውጤት |
|---|---|---|
| በቅርቡ የተዋወቃቸው ሰዎች<br>ቤተክርስቲያን ለመትከል ታስቦ ወንጌልን ለማድረስ የተዋወቃቸው ሰዎች | | |
| ወደጌታ የመጡ አዳዲስ ሰዎች<br>የኢየሱስ ተከታዮች | | |
| በቅርብ የተጠመቁ ሰዎች<br>በጥምቀት ስርአት የተሳተፉ ሰዎች | | |
| በስልጠና ላይ ያሉ አዳዲስ መሪዎች<br>ለቤተክርስቲያን ተከላ የሚመለመል ሰው ለመሪነት የሰለጠነ ነው | | |

**አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች የሚሳተፉበት ቡድን፤ በትንሹ ሁለት ደቀመዝሙር እና አንድ መሪ**

| | ወርሃዊ ግብ | ወርሃዊ ውጤት |
|---|---|---|
| አዳዲስ ትናንሽ ቡድኖች<br>በዚህ ወር የተጀመሩ ቡድኖች | | |
| በትናንሽ ቡድኖች የተካተቱ አዳዲስ ተሳታፊዎች<br>በዚህ ወር በትናንሽ ቡድኖች መሳተፍ የጀመሩ አዳዲስ ሰዎች | | |
| የቡድን መሪ የሆኑ አዳዲስ መሪዎች<br>በቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ ክትትል የሚደረግለት ቡድን መሪ የሆነ አዲስ መሪ | | |

## የጸሎት ርዕስ

1. ______________________________
2. ______________________________
3. ______________________________

## ምስክርነት

ከዚህ በታች ያለው ክፍት ቦታ የመጨረሻ ሳይሆን እንደመነሻ የቀረበ ሲሆን ተጨማሪ ወረቀት መጠቀም ይቻላል

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

# ክፍለትምህርት 1

# እግዚአብሔር እያሳየኝ ያለው ነገር፡-

## የጥናትና ምርምር ውጤትህን ለሌሎች ማካፈል (60 ደቂቃ)

የአሰልጣኙ መምሪያ፡- እንዲህ በል "በሞጁል 1 ለሞጁል 2 የተገበሩ እቅድ፡- "የመጨረሻ" አዳችሁ የሚለውን እንድታሟሉ ተጠይቃችሁ ነበር፡፡ በሞጁል 2 ደግሞ በተክርስቲያን ለመትከል ያሰባችበትን ስፍራ እንድትሰልሉ/እንድታጠኑ ተጠይቃችኋል፡፡ ጥናትና ምርምራችንን በጥልቀት ከማከሄዳችን በፊት፤ ከዚህ በፊት የሰራችሁትን የቤትስራ ሪፖርት የምታደርጉበት ጥቂት ጊዜ ውሰዱ፡፡"

- ተሳታፊዎችን ሁለት ሁለት ወይንም ሶስት ሶስት አድርገ በመመደብ እያዳንዱ ተሳታፊ 15 ደቂቃ ወስዶ ለቡድኑ በሞጁል 2 ላይ ለሞጁል 3 የተገበሩ ዕቅድ የቤትስራ ያደረገውን ጥናትና ያገኘውን ውጤት በተዘጋጀው የሪፒርት ቅጽ መሰረት ያቅርብ፡፡ ቅጹ ከዚህ በታችም ቀርቧል፡፡
- እያንዳንዱ ቡድን ተራ በተራ አተገባበራቸውን ያዩ ዘንድ ቅደም ተከተል ስራላቸው፡፡
- የቤትስራቸውን ያልሰሩ ተሳታፊዎች ካሉ በአረፍት ሰአታችሁ ጥቂት ጊዜ ወስደህ አነጋግራቸው፡፡ የቤትስራቸውን የሚቀጥለው ስለጠና ከመጀመሩ በፊት ጨርሰው እንዲያስገቡ እቅድ እንዲያወጡ አድርግ፡፡
- የመጨረሻዎቹን15 ደቂቃዎች ለተሳታፊዎች ስለቤትስራው የምታስረዳበት ጊዜ ይሁን፡፡

እያንዳንዱ ተሳታፊ ሪፖርት የሚያደርገው ከ10-15 ደቂቃ ባለ ጊዜ ውስጥ ሲሆን የሚከተሉትን መረጃዎች ማካተት ይጠበቅበታል፡-

## 1. ክፍል አንድ፡- የተሰበሰበው ወሳኝ መረጃ (5-7 ደቂቃ)

የመረጥከውን አካባቢ ግለጽ፡፡

- አንዴት ነው መረጃህን የሰበሰብከው (በዳሰሳ ጥናት፣ መደበኛ ያልሆነ ቃለመጠይቅ፣ ምስከታ/ካርታ መስራት፣ ቤተመጽ ሐፍት የሚገኝም መረጃ መመርመር፣ ወ.ዘ.ተ...)?
- ስለገጠሙህ ተግዳሮቶች ወይንም ችግሮች እና እንዴት እንዳለፍካቸው አስረዳ፤ በሚቀጥለው ጊዜ በተለየ ልትከውን የምትችለው ነገር ምንድን ነው?

## 2. ክፍል ሁለት፡- መረጃን መተንተን (5-8 ደቂቃ)

ቀሪው የሪፖርት ጊዜ መሆን ያለበት የትኛትና ምርምር ውጤትን ለመተንተን ነው፡፡ ሪፖረቱ የሚከተሉትን ቁልፍ ጥያቄዎች የሚመልስ መሆን ይጠበቅበታል፡-

- ስለመረጥከው አካባቢ እና በዚያ ስለሚኖሩ ሰዎች የተማርከው አስገራሚ መረጃ ምን ነበር?
- ያስገረመህን መረጃ ለጥናትና ምርምሩ ወቅት አገኝተሃል?
- በመረተከው አካባቢ ቤተክርስቲያን ለመትከል የሚያስችል አንድ የተለየ ምክንያ ሊሆን የሚችል መረጃ አገኝተሃል?
- ምንአይነት መረጃ ነው ስለ መኸር መስክህ አንተ ከዚህ ቀደም የምታውቀው እና በዚህ ጥናት የተረጋገጠለህ?
- ለወንጌል በር ሊገፋት የሚችል ምን አይነት አጋጣሚ እንዳለ ተገነዘብክ?
- ምን አየንተለ እንቅፋቶች እንዳሉ እና እንዴት ሊታለፉ እንደሚችሉ ተገነዘብክ?
- በመረጥከው አካባቢ ሁሉን አቀፍ ወንጌል ስርጭትና የቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት እንዲኖር ምን አይነት ተጨማሪ ጥናቶች መደረግ እንደሚገባቸው ተገነዘብክ?

# ክፍለትምህርት 2

# እግዚአብሔር እያሳየኝ ያለው ነገር፡-

## የጥናትና ምርምር ውጤትህን ለሌሎች ማካፈል (60 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** እንዲህ በል "በሞጁል 1 ለሞጁል 2 የትግበራ እቅድ፡- "የመጨረሻ" እዳችሁ የሚለውን እንድታሚሉ ተጠይቃችሁ ነበር፡፡ በሞጁል 2 ደግሞ በተክርስቲያን ለመትከል ያሰባችበትን ስፍራ እንድትሰልሉ/እንድታጠኑ ተጠይቃችኋል፡፡ ጥናትና ምርምራችንን በጥልቀት ከማከሄዳችን በፊት፤ ከዚህ በፊት የሰራችሁትን የቤትስራ ሪፖርት የምታደርጉበት ጥቂት ጊዜ ውሰዱ፡፡"

- ተሳታፊዎችን ሁለት ሁለት ወይንም ሶስት ሶስት አድርገ በመመደብ እያዳንዱ ተሳታፊ 15 ደቂቃ ወስዶ ለቡድኑ በሞጁል 2 ላይ ለሞጁል 3 የትግበራ ዕቅድ የቤትስራ ያደረገውን ጥናትና ያገኘውን ውጤት በተዘጋጀው የሪፒርት ቅጽ መሰረት ያቅርብ፡፡ ቅጹ ከዚህ በታችም ቀርቧል፡፡
- እያንዳንዱ ቡድን ተራ በተራ አተገባበራቸውን ያዩ ዘንድ ቀደም ተከተል ስራላቸው፡፡
- የቤትስራቸውን ያልሰረ ተሳታፊዎች ካሉ በእረፍት ሰአታችሁ ጥቂት ጊዜ ወስደህ አነጋግራቸው፡፡ የቤትስራቸውን የሚቀጥለው ስለጠና ከመጀመረ በፊት ጨርሰው እንዲያስገቡ እቅድ እንዲያወጡ አድርግ፡፡



- የመጨረሻውን 15 ደቂቃዎች ለተሳታፊዎች ለቤትስራው የምታስረዳበት ጊዜ ይሁን፡፡

# ክፍለትምህርት 3

## ቤተክርስቲያን የመትከል መሪ እቅዱ፦ የእግዚአብሔርን ራዕይ በመንፈስ መረዳት (60 ደቂቃ)

**እንዴት የራዕይ ገላጭ አርፍተነገር መጻፍ ይቻላል (5 ደቂቃ)**

**የአሰልጣኙ መመሪያ፦** ከታች የቀረበውን መረጃ በመጠቀም የራዕይን ጽንሰ ሐሳብ ገላጭ አርፍተነገር እንዴት ማዘጋጀት እንደሚቻል አስረዳ፡፡ ይህን በምታደርግበት ወቅት ተሳታፊዎችም በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ ያለውን ክፍት ስፍራ በተገቢው ቃላት እንዲሞሉ አሳስባቸው፡፡

ራዕይ ገላጭ አርፍተነገር ማለት ግልጽ በሆነ እና ቀለል ባለ የቃላት አጠቃቀም <u>እግዚአብሔር</u> የምንመራው ቤተክርስቲያን ምዕመናን እንዲሆኑለት የሚፈልገውን <u>ዝርዝር</u> ማስቀመጥ ማለት ነው፡፡ ራዕይ የቤተክርስቲያኒቱን መኖር ጠቅለል አድርጎ የሚያሳይ ምስልን የሚከስት እና ቤተክርስቲያኒቱ መሳ አቅሟን ያለማንደል ብትጠቀም የምትደርስበትን ምናባዊ ግብን የያዘ ሆኖ፤ የምዕመኗን ተግባር ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይም መሆን ይኖርበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ቤተክርስቲያኒቱ <u>ወደፊት</u> ልትደርስበት ያሰበችውም የሚያሰይ መሆን ሲኖርበት ከዚኅ ቀደም ያስመዘገበችውን ድል ብቻ የሚያሳይ መሆን የለበትም፡፡

ቤተክርስቲያን ለመትከል ላሰባችሁት ስፍራ የሚጠቅም እንዲሆን ራዕይ ገላጭ አርፍተነገራችሁ በጥናት ያገኛችሁትን እና የተማራችሁበትን መረጃ ማካተት ይኖርበታል፡፡

**ራዕይ ገላጭ አርፍተነገር አጻጻፍን የሚያሳዩ አራት ምሳሌዎች (15 ደቂቃ)**



1. "በመንፈስ ቅዱስ የተሞላና ክርስቶስን ወደመምሰል የሚያድግ ቤተክርስቲያን መሆን"
2. "በማህበረሰባችን ጨለማ ላይ የሚያበራ የክርስቶስ መብራት መሆን"
3. "የክርስቶስን ጽድቅ እና ተስፋ ለምዕመናች፣ ለከተማችን እና ለተቀረው አለም ሁሉ የሚያንጸባርቅ የእምነት እና ጽድቅ ማህበረሰብ መሆን"
4. "የጠፋትንም ሆነ የእኛ የሆኑ አማኝ ወገኖችን፣ በአካባቢያችን የሚገኙ ሰዎችን እና በአለም ዙሪያ ያሉትን ሁሉ የሚያገለግል ጽድቅና ታኝነት የሞላበት ማህበር መሆን።"

ከላይ ያነሳናቸው ራዕይ ገላጭ አርፍተነገሮች እግዚአብሔር በቅዱስ ቃሉ የእርሱ የሆነች ቅድስት ቤተክርስቲያን መሆን የሚገባትን የሚያንጸባርቁ መሆናቸውን ልብ ይሏል። ይሁን እንጂ ሁሉም ራዕይ ገላጭ አርፍተ ነገሮች ራዕይን በመግለጡ ረገድ እኩል አይደሉም።

1. **የመጀመሪያው አርፍተነገር** በከፊል የቤተክርስቲያኒቱን ነባራዊ ሁኔታ የሚያሳይ ሲሆን ወደፊት ሊደርሱበት እና ሊያሻሽሉት የሚጋባን ጉዳይንም አስቀምጧል። ይህ አርፍተነገር የማህበርዕመኑ መገለጫ የሆነ ባህሪን ወይንም የአገልግሎቱን ተግባር ምን ላይ እንደሚያተኩር አይገልጥም።

2. **ሁለተኛው አርፍተነገር** ብዥታን የሚፈጥር እና በማንኛውም ጊዜና በየትኛውም መንገድ እውነት ሊሆን የሚችል ነው። ከዚህም በተጨማሪ የማህበረምዕመኑ መገለጫ የሆነ ምንም አይነት የባህሪም ሆነ የአገልግሎት ትግበራ ሂደት ማሳያ የለውም።

3. **ሶስተኛው አርፍተነገር** በመጠኑም ቢሆን ሙሉ ሊባል የሚችል ነው፤ ማህበረ ምእመኑን ባህሪ እንዲህ ገልጦታል (ጻድቅና በክርስቶስ ተስፋ ሚያደርግ)፤ የት እንደሚያገለግሉ ሲገልጥ ደግሞ (ምዕመኑን፣ ከተማውን እንዲሁም የተቀረውን ዓለም) ብሎ አስቀምጦታል። የማህበረ ምዕመኑ ባህሪያትም ሆነ ቤተክርስቲያኒቱ በአገልግሎት ለመድረስ ያስቀመጠችው ግብ ሁለቱም የወደፊቱን ስራ ግብአትን የሚያመለክቱ ናቸው።

4. **አራተኛው አርፍተነገር** ከሁሉ በተሻለ ሙሉ ነው። አርፍተነገረ የማህበረ ምዕመኑንባህሪ፣ አገልግሎቱ ተደራሽ የሚያደርጋቸውን የማህበረሰብ ክፍሎች እና ቤተክርስቲኒቱ በካል ልትገኝ

የምትችሉባቸው ስፍራዎችን ለአንባቢው የሚያሳ ነው። እነዚህ ምናባዊ ራዕይ መገለጫዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይዘት ያላቸው ናቸው።

## ተግባራት (40 ደቂቃ)

1. በትናንሽ ቡድኖች ወይንም ጥንድ ጥንድ በመሆን እናት የመሰረታችሁት ወይንም ልትመሰርቱት ያሰባችሁት ቤተክርስቲያን እንዲስና በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ ሙሉ እንደሆነ በማሰብ፤ እግዚአብሔር ቤተክርስቲያኒቱን ሲገልጡ የሚችሉ ቃላትን መዝግቡ። ለምሳሌ እንዲህ የሚሉ ቃላትን መጠቀም ትችላላችሁ፡- ጻድቅ፣ ታማኝ፣ አፍቃሪ፣ ደስተኛ፣ ሩህሩህ፣ ለጋስ ወ.ዘ.ተ…እንዚህ ቃላት የሚገልጡት የማበረምዕመኑን ባህርይ ነው። እነዚህን የዘረዘርናቸውን ቃላትን ከዚህ በታች ያለውን አርፍተነገር ለመጨረስ ተጠቀምበት።

እግዚአብሔር ____________________________________________

________________________________________ እንድንሆን ይፈልጋል።

2. ቀጥሎ የቀረበውን አርፍተነገር ለትሞላ ማንን ለማገልገል እንደተጠራህ ግለጽ፡-

እግዚአብሔር እንድናገለግል የሚፈልገው….(ማንን ነው?)

____________________________________________________

____________________________________________________

3. በመጨረሻም ልትተክሉት ያሰባችሁት ቤተክርስቲያን በሙሉ አቅሙ ሲሰራ ወይንም በምናባችሁ ያሰባችሁት ቦታ ላይ ቢደረስ ምን ሊሰራ እንደሚችል የሚያሳዩ ተግባራትን ዘርዝሩ፡

- ወንጌልን ለዓለም ሁሉ ማድረስ
- በሁሉም የእድሜ ክልል ያሉ የማህበረሰባችን ክፍሎችን ማገልገል
- ሁሉን ማህበረ ምዕመን መንፈሳዊ በሆነ ደቀመዝሙርነት ማስገባት

- ያልተቋረጠ የገንዘብ አቅምን መገንባት

እነዚህን ተግባር አመልካች ሃረጎች የሚከተለውን አርፍተነገር ሙሉ ለማድረግ በመጠቀም መዘርዘር ትችላላችሁ

4. ባህርያችንን የምንገልጸው....

---

---

---

5. ልትመሰረት ያሰብከው ቤተክርስቲያን ማህበረ ምዕመናን ምናባዊ ባህርይ እና ቤተክርስቲያን ለማገልገል ያሰበችው ማህበረሰብ ይገልጣል ብለህ ያሰብከውን ቃልና የማበረ ምዕመኑን ተግባራት የሚጠቁመውን ሐረግ አብረውህ ከሚሰሩ ሰዎች ጋር ወይንም ከጥናት ቡድንህ ጋር ተወያይበት፡፡ከተዘረዘሩት ውስጥ በጣም አስፈላጊ ብላችሁ የመረጣችኋቸው ሶስቱን ጻፉ፡-

---

---

---

6. በመጨረሻ፤ በጣም አስፈላጊ የመትላቸውን ገላጭ ቃለት፣ የአገልግሎቱ ተደራሾች እና ተግባር አመልካች ሐረጎችን በመጠቀም ራዕይ ገላጭ አርፍተነገር ስራ፡፡ (እንደምሳሌ ከቀረቡት ራዕይ አመልካች አርፍተነገሮች ሶስተኛውን ወይንም አራተኛውን መጠቀም ትችላለህ፡፡)

---

---

---

የጻፍከውን ራዕይ አመልካች አርፍተነገር ለጠቅላላው ተሳታፊ በማካፈል፤ የተጠቀምክባቸው ቃላት ግልጽ እንደሆኑ እና አሳብህንም በትክክል እንደገለጹልህ አስተያየት እንዲሰጡህ አድርግ።

7. ተሳታፊዎች የሰጡህን አስተያየት በማካተት የተጠናቀቀውን ራዕይ አመልካች አርፍተነገር እዚህ ክፍት ቦታ ላይ አስፍር።

8. ይህን ራዕይ የሚደግፉ የትኞቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ናቸው?

9. ራዕይ ገላጭ አርተነገርህን ደግመህ በማጥራት በቀላሉ ሊረዱት የሚችልና ግልጽ እንዲሆን አድርግ። እንዴት አድርገህ ነው ይህን ራዕይ አገልግሎትህን በይፋ ለማስጀምር የምትጠቀምበት እና በጅማሮ ለመሳተፍ የጋበዝከው ቡድን አባላት እነዴት ራዕዩውን የራሳቸው እንዲያርጉ ታስችላቸዋለህ? ማህበረምዕመኑስ ይህን ራዕይ የራሱ እንዲያደርግ እና እንዲደግፈው ማወቅ እና ማመን የሚፈልገው ጉዳይ ምንድን ነው? እንዴትስ አድርገህ ማህበረ ምዕመኑ ይህን እንዲያደርግ ተረዳዋለህ?

# ክፍለትምህርት 4

# ቤተክርስቲያን የመትከል መሪ እቅዱ፡-

## ተልዕኮን መተርጎም (60 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** ከዚህ በታች የቀረበውን አሳብ ተልዕኮ ገላጭ አርፍተነገርን ለማስረዳት ተጠቀምበት፡፡ ከዚያም ተሳታፊዎች ቀጥሎ ያለውን ተግባር እንዲያጠናቅቁ ምሩቸው፡፡

### ተልዕኮ ገላጭ አርፍተነገር እንዴት መጻፍ ይቻላል

ምልከታ እና አዲስ ጽንሰ አሳብ (15 ደቂቃ)



**ምልከታ**

ራዕይ ገላጭ አርፍተነገር ማለት እግዚአብሔር ማህበረምዕመኑ እንዲሆንለት ይፈልጋል ብለህ ያመንከውን መግለጥ ነው፡፡ ራዕይ፤ ማህበረ ምዕመኑ ወደፊት ሲሆነው ያለውን አመልካች ነው፡፡

**አዲስ ጽንሰ አሳብ**

**ተልዕኮ ገላጭ አርፍተነገር ቤተክርስቲያኒቱ ራዕይ ላይ ያስቀመጠችውን እቅድ እንዴት አድርጋ ራዕዩዋን እውን ልታደርግ እንደምትችል ጠቅለል አድርጎ የሚያሳይ ነው፡፡**



ተልዕኮ ገላጭ አርፍተነገር፤ ራዕይን እውን ለማድረግ የሚደረግን ተግባር ምን እንደሆነ የሚነገር ነው፡፡

**ተልዕኮ ገላጭ አርፍተነገር ማለት ተግባር ገላጭ አርፍተነገር ማለት ነው፡፡**

ቤተክርስቲያን ለመትከል ሳለባችሁት ለፍሬ የሚጠቅም እንዲሆን ተልዕኮ ገላጭ አርፍተነገራችሁ በጥናት ያገኛችሁትን እና የተማራችሁበትን መረጃ ማካተት ይኖርበታል፡፡

1. የሕይወት ውሃ ቤተክርስቲያን ተልዕኮ፤ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ለሉስ አካድ የሆነውን እግዚአብሔርን በማምለክ፣ ቅዱስ ቃሉን በመስበክ፣ ለቅርብ አካባቢያችን ግልጋሎት በመስጠት፣ ያመኑትን ሁሉ ከልጅ እስከ አዋቂ ደቀመዝሙ በማድረግ እና የእግዚአብሔር ቤተሰብ አንድነትን በመጠበቅ መኖር ነው፡፡
2. በአዲስ ሕወት ማህበረሰብ ቤተክርስቲያን፤ ከዚህ በታች ባሉት መንገዶች የክርስቶስን ብርሃን እናንጸባርቃለን፡-
   - እውነተኛውን አምላክ በእውነት እና በመንፈስ ማምለክ (ዮሐ 4፡24)
   - በቤተክርስቲያን ውስጥ እና ከቤተክርስቲያን ውጪ የእግዚአብሔርን ቃል በማያሻመ ሁኔታ/ለሁሉ ግልጽ በሆነ ሁኔታ መስበክ (ማቴ 28፡18-20)
   - የቅርብ አካባቢያችንን እና ቤተሰባችንን፣ የተናቁና የተገፉ እንዲሁም የተረሱ የማህበረሰባችንን ክሎች፣ በክርስቶስ ፍቅር ማገልገል (2ጴጥ 3፡18)፡፡
   - በጌታ ወንድም እና እህቶቻችንን በክርስቶስ ፍቅር ማገልገል (ሮሜ 12፡10፣13)

## ተግባራት (45 ደቂቃ)

1. ከላይ በቀረቡት ተልዕኮ ገላጭ አርፍተነገር ምሳሌዎች መሰረት፤ የማህበረ ምዕመኑ ተግባር ምንድን ነው?

---

---

---

2. ከዚህ በታች ባለው ክፍት ቦታ ላይ (ከዚህ በፊት በመማሪያ ደብተርህ ላይ ያሰፈርከውን) ራዕይ ገላጭ አርፍተነገር ጻፍ።

3. ቤተክርስቲያናችሁ የትኛውን ማህበረሰብ ነው መድረስ የምትፈልገው?

4. እንዴት ነው ማህበረ ምዕመኑ ለደርስ ያሰበውን ማህበረሰብ የመድረስ ራዕይ እውን ለማድረግ የሚችለው?

እያንዳዱ ተልዕኮ ገላጭ አርፍተነገር አምስቱን የመቤተክርስቲያን ተግባራት ያካተተ እንዲሆን እንመክራለን።

- ስብከት እና ወንጌል ስርጭት
- ትምህርት እና ደቀመዝሙርነት
- ግልጋሎት

- ህብረት
- አምልኮ

5. ተልዕኮ ገላጭ አርፍተነገር ራዕያችንን እንዴት ልንፈጽም እንደቀድን የሚነግር ነው። ታዲያ ተልዕኮ ገላጭ አርፍተነገራችሁን በምትሰሩበት ወቅት እያንዳንዱ ተግባር (በእግዚአብሔር ኃይል!) እንዴት ራዕያችሁን ለመፈጸም እንደሚያግዛችሁ ማሳየታችሁን አትዘንጉ። ጀመራችሁትን ተልዕኮ ገላጭ አረፍተነገር በማጠናቀቅ ከዚህ በታች አስፍሩ።

6. የትኞቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተልዕኮ ተኮር ተግባርህን ይደግፉልሃል?

7. የጻፍከውን ራዕይ እና ተልዕኮ ገላጭ አርፍተነገር (ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃው ጋር) ለጠቅላላው ተሳታፊ ካቀረብክ በኋላ ከዚህ በታች ባለው ስፍራ ላይ በጽሑፍ አስፍር።

# ለሞጁል 4 የሚሆን የትግበራ እቅድ

ራዕይ እና ተልዕኮ ገላጭ አርፍተነገርህን ለ መጋቢህ እና ለምትደግፍህ ቤተክርስቲያን አቅርብ፡፡

ወደ ሞጁል 4 ከመሻገርህ በፊት፤ ራዕይ እና ተልዕኮ ገላጭ አርፍተነገርህን (ከነመጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃው) አገልግሎትህን በይፋ ለማስጀመር ለሰበሰብከው ቡድን፣ ለእናት ቤተክርስቲያንህ እና በማማከርና ድጋፍ ለሚያገለግልህ ግለሰብ አቅርብ፡፡ የሚቻል ከሆነ መጋቢህ በአምስቱ የቤተክርስቲያን ቁልፍ ተግባራት ተካታታይ ትምህርት እንዲያስተምርና ማህበረ ምዕመኑን ራዕይ እና ተልዕኮውን በሚገባ እንዲረዳውና የራሱ  እንዲያደርገው ማድረግ፡፡

ራዕይ እና ተልዕኮህን በምታቀርብበትጊዜ ማህበረ ምዕመኑ እንደሚስማሙባቸው እና ለመደግፍ ፍቃደኛ እንደሆኑ ጠይቅ፡፡ ለዚህ ተግባር በፈቃደኝነት ራሳቸውን ለመስጠትና አብረው ለመስራት የሚፈልጉ ሰዎች ካሉ ጥሪ አቅርብላቸው እና አብራችሁ ለመስረት ተዘጋጁ፡፡

አገልግሎትህን በይፋ ለማስጀመር የመረጥከው ቡድን እና እናት ቤተክርስቲያንህ በመሪዎች የተሰጠውን ትርጉም የማይቀበሉ ከሆነ፤ አገልግሎትህን ለመጀመርም ሆነ በዚያ ለመዝለቅ ለስሚከብድ ራዕይህን በተልዕኮ ለመፈጠም የሚረዳ ለውጥ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ምንም አይነት ለውጥ ከመደረጉም በፊት አገልግሎቱን ለማስጀመር የተመረጠው ቡድን፣ የእናት ቤተክርስቲያን መሪዎች እና ቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ መወያየት እና መግባባት ላይ መድረስ ያስፈልጋቸዋል፡፡

# ክፍለትምህርት 5

# ቤተክርስቲያን የመትከል ሙሉ እቅዱ:-

# እሴትን መተርጎም (60 ደቂቃ)

የአሰልጣኙ መምሪያ:- ከታች የቀረበውን መረጃ በመጠቀም የእሴትን ጽንሰ ሀሳብ ገላጭ አርፍተነገር እንዴት ማዘጋጀት እንደሚቻል አስረዳ፡፡ ይህን በምታደርግበት ወቅት ተሳታፊዎችም በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ ያለውን ክፍት ስፍራ በተገቢው ቃላት እንዲሞሉ አሳስባቸው፡፡

## እሴት ገላጭ አርፍተነገር እንዴት መጻፍ/ማዘጋጀት ይቻላል (15 ደቂቃ)፡፡

ክለሳ እና አዲስ ጽንሰ ሀሳብ

**ክለሳ**

ራዕይ እግዚአብሔር እንድትሆንለት የሚፈልገው ገላጭ ነው፡፡

ተልዕኮ እግዚአብሔር እንድትሰራለት የሚፈልገውን ገላጭ ነው፡፡

**አዲስ ጽንሰ ሀሳብ**

እሴት የሚገልጠው ራዕይህን ለማሳካት በምትተገብረው የተልዕኮ ስራ እንዴት መልካም ባህርይ ታሳያለህ የሚለውን ነው፡፡

## ሁለቱ የእሴት ገላጭ አርፍተነገሮች ናሙና፡- (30 ደቂቃ)

### 1. የመደን አለት ቤተክርስቲያን እሴቶች (በድርጊት ገላጭ ቃለት ሲቀመጡ)

**የእግዚአብሔር ሕዝብ አንደመሆናችን፤ ራሳችንን ለእነዚህ እሴቶች ሰጥተናል፡-**

- አንደ ግለሰብ እና እንደማህበረሰብ ክርስቶስን ለመምሰል አንተጋለን (ሮሜ 8፡29፤2 2ቆሮ 3፡18)።
- እውነትን በፍቅር እንናገራለን (ኤፌ 4፡15፣ 25፣ 29)፣ በመገለጽ እና በማቅናት እንዲሁም እያንዳንዱን ውሳኔ ለን የገንዘብ ፍሰት በግልጽነት እናሳውቃለን።
- አንዳችን ሌላችንን በፍቅር እናገለግላለን፣ የእያንዳንዱን ሰው ጸጋ አንለያለን ደግሞም በጸጋቸው ያገለግሉ ዘንድ እድሎችን እንፈጥራለን (ሮሜ 12፡1-8፤ 1ጴጥ 4፡10-11) አንዲሁም ቤተኛውም እድሜ ወደጊታ የመጡ አባሎቻችንን ደቀመዝሙር እናደርጋለን(ዘዳ 6፡20፤ 11፡18-21፤ ማቴ 28፡18-20)።

### 2. የሕይወት ውሃ ቤተክርስቲያን እሴቶች (በስም እና ድርጊት ገላጭ ቃለት ሲቀመጥ)

**አንደ ክርስቲያን ማህበረሰብ፤ የሚከተሉት እሴቶቻችን ናቸው፡-**

- ግልጽ እና ጠቃሚ የሆነ የቃለ እግዚአብሔር ስብከት (ማቴ 28፡18-20፤ 2ጢሞ 4፡2)
- አምልኮአችን ስሉስ አሃድ የሆነውን አምላክ ማዕከል ያደረገ አንጂ የእኛን ፍላጎት ማዕከል ያደረገ አይደለም (ዘዳ 5፡6-10)
- በቤተክርስቲያናችንም ውስጥ ይሁን ከቡተክርስቲያነችን ውጪ ያሉ እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ሰዎች ማገልገል (ማር 12፡31፤ ኤፌ 5፡1-2)
- ምዕመናን ከልጅ እንከ አዛውንት ደቀመዝሙር ማድረግ (ማቴ 28፡18-20፤ ዘዳ 6፡20፤ 11፡18-21)

- በክርስቶስ ወንድም እና እህት የሆኑን ሰዎች ማወቅ እና መንከባከብ (ኤፌ 4፡2፣ 25-32)
- አገልጋይ መሪነት እና ጸጋውን የሚጠቀም ምዕመን (ማቴ 20፡25-28፤ 1ጴጥ 4፡10-11)
- ኃላፊነት የሚሰማው የንብረት ባለአደራ (መዝ 24፡1)

የተለመደው የአንድ ድርጅት/ቤተክርስቲያን እሴት ገላጭ አርፍተነገሮች ብዛት ከሶስት እስከ ሰባት ነው። ታዲያ እነዚህ እሴት ገላጭ አርተነገሮች ለማስታወስ ይደዳ ዘንድ በጣም አጭር መሆን ይጠበቅባቸዋል።

በአብዛኛው በእሴቶች ውስት የሚጠቀሱት ተግበሩ በተለዕኮ ገላጭ አርፍተነገሮች ውስጥ የተገለጡ ናቸው። ልዩነታቸው የሚሆነው በእሴቶች ውስጥ የሚገለጡት ተግባሩት የሚመነጩት አንድ ባህሪን ከመላበስ እና ከመጠቀም ውስጥ ነው። ለምሳሌ የሕይወት ውሃ ቤተክርስቲያን እሴት "አምልኮ" የሚለን ተግባር ብቻውን ከማስቀመት ይልቅ ወሳኝ የሚባለን የአምልኮ አየነት ያሳያል፤ ከሰዎች ፍላጎት ይልቅ በእግዚአብሔር ስሉስ አሃድነት ላይ ያተኮረና የጽድቅ ባህርይን የሚያንጸባረቅ በማለት ያቀርበዋል። እሴቶች ቤተክርስቲያን መሪወች ማህበረ ምዕመኑን የተመከተ ውሳኔ፣ መሪወችን መገምገም፣ ማህበረን ማገልገል ወ.ዘ.ተ... በሳቡ ጊዜ ሁሉ ከግምት ውስጥ የሚያስገቡት መጠበቂያ ነው።

ሁሉም ለሴቶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረት ሊኖሩቸው እና በመጽሐፍ ቅዱስ ቀጥተኛ ድጋፍ ወይንም መርህ ኖሯቸው መታቀድ አለባቸው።

እሴቶቻችሁ በአስፈላጊነት ቅደም ተከተል እንዲሰፍሩ አንመክራለን። በአብዛኛው ውጤታማ መሪነት በሰዎችም ይሁን በድርጅት የሚከሰቱ ተወዳዳሪ እሴቶች መካከል ቀዳሚውን ለይቶ ማውጣት እና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ መቻል ነው። ለምሳሌ፡- በእሴት ቁ. 5 ላይ ያለውን በተመለከተ እሴት ቁ.1 ላይ ያለው ለጊዜው እንዳይተገበር የሚያስገድድ ውስኔ ቢያስፈልገው ወይንም ቁ.5

ቀዳሚ ተግባር እንደሆነ ቢወሰን፤ ማህበረምዕመኑ ለዚህ እሴት ተገዢ ይሆን ዘንድ በቁ.1 ላይ ያለው ቁ. 5ን እንዲደግፍ ድግ መሰራት (አንዳንዴም ከነአካቴው መወገድ) ይኖርበታል።

## ለሞጁል 4 የሚሆን የትግበራ እቅድ

አዲስ ለተተከለው ላሰብከው ቤተክርስቲያን እሴት ምን ሲሆን እንደሚገባ ወስን (15 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** የሚሰጠውን የቤት ስራ መመሪያ ለተሳታፊዎች በማንበብ ያላቸውን ጥያቄ በሙሉ ለመመለስ ሞክር።

1. ከመጋቢህ፣ ድጋፍ ከምታደርግልህ ቤተክርስቲያን እና ከአዲሱ ቤተክርስቲያን አባላት (ቤተክርስቲያን ከተከልክ) ጋር በመሆን እሴቶችን ለማዘጋጀት በጋራ ስሩ። ከ5-9 የሚሆን ሰው በጋር እንዲሰራ እንመክራለን። ጠቅላላውን ተሳታፊ ሶስት ሶስት ወይንም አራት አራት አድርጎ በመመደብ ለእያንዳንዱ ቡድን የሚከተሉት ይከወናሉ፡-

- ራዕ እና ተልዕኮ ገላች አርፍተነገርህን እንደገና አንብብ
- ሁለቱን የእሴት ገላጭ አርፍተነገሮች ናሙና እንደገና አንብብ። ከእነዚህ ምሳሌዎች ምናልባት ለቤተክርስቲያንህ የምታስባቸው እሴቶችምን መሆን እንዳለባቸው ምሪት ሊሰጡህ ይችላል።
- እንደ አንድ የአማኞች ስብስብ እንዴት አድርጋችሁ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረት ያለውን አስፈላጊ እሴት መለየት እና በዚያ መኖር እንደምትችሉ ግለጹ። (በቤተክርስቲያናችሁ ባህል አውድ እና ከላ እንደምሳሌ ከቀረቡት እሴት አመልካች አረፍተነገር ምሳሌዎች ሌላ መጨመር የሚገባው ወይንም ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው እሴት ካለ አረጋግጡ)
- በመጪው አመት መሪዎች እና ምዕመኑ በጠቅላላ ምን አይነት ተግባር መከወን እንደሚገባቸው የሚጠቁሙ ከ5-7 የሚሆኑ እሴቶችን ምረጡ። በዚህ ረገድ ሊመረጡ የሚችሉ ብዙ እሴቶች ቢኖሩም በቅድሚያ ግን አሁል ላለነበት ቤተክርስቲያን የሚሆን እና እየሰራህ ያለኸውን ራዕይ እና ተልዕኮህን የሚደግፍልህን ምረጥ።

2. እያንዳንዱ ቡድን ያዘጋጀውን እሴት ገላጭ አርፍተነገሮች እንዲያቀርብ አድርግ፤ ከዚያ ለእነዚህ እሴቶች የሚሆን መጽሀፍ ቅዱሳዊ መሰረቶችን ፈልግ፡፡

3. አንድ ላይ በመሆን ከ5-7 የሚሆኑ እና ቤተክርስቲያንና ማህበረ ምዕመኑ ለመጪው ሶስት ወይንም አምስት አመታት ምን መተግበር እንዳለባቸው የሚያሳዩ እሴቶችን ምረጡ፡፡

4. ያዘጋጀኸውን እሴት ገላጭ አርፍተነገሮች ለማህበረ ምዕመንህ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረታቸው እና ለምን እያንዳንዱ እሴት እንዲመረጥ ካደረገው መሰረታዊ ምክንያት ጋር አቅርብ፡፡ ከዚያም አባላቱ በእነዚህ እሴቶች ላይ አሳብ እንዲሰት አድርግ፡፡ እንደየአስፈላጊነቱ እሴቶቹን አሻሽል፤ ነገርግን እያንዳንዱ እሴት መጽሐፍ ቅዱስን መሰረት ያደረገ መሆን ይገባዋል፡፡

5. እያንዳንዱ የቤተክርስቲያን አባል ለእነዚህ እሴቶች ተገዢ እንዲሆን እና በዚህ መሰረት እንዲኖር እድል ፍጠርላቸው (ለምሳሌ፡- እሴቶችን ለማስተዋወቅ ብቻ የሚሆን አንድ ፕሮግራም ማዘጋጀት)፡፡

6. ሞጁል 4ን መማር ስትዘጋጅ በዚያው እሴቶችህንም ለተሳታፊዎች ለማቅረብ ተዘጋጅ፡፡ ይህም ብቻ ሳሆን እሴቶችህን ለማዘጋጀት የተጠቀምክበትንም ሂደት ለውይይት ለማቅረብ ተዘጋጅ፡፡

**እሴት ገላጭ አርፍተነገሮችህን አስፈፍር፡-**

(15 ደቂቃ ረፍት)

# ክፍለትምህርት 6

# ቤተክርስቲያን የመትከል መሪ እቅድ፡-

# ስልትን መተርጎም (60 ደቂቃ)

**ክለሳ እና አዲስ ጽንሰ ሐሳብ (15 ደቂቃ)**

**ክለሳ**

**ራዕይ፤** እግዚአብሔር <u>እንድትሆንለት</u> የሚፈልገው ገላጭ ነው።

**ተልዕኮ፤** እግዚአብሔር <u>እንድትሰራለት</u> የሚፈልገውን ገላጭ ነው።

**እሴት፤** እግዚአብሔር ምን አይነት ባህሪ እንድታንጸባርቅ እንደሚፈልግ ይገልጣል።

**አዲስ ጽንሰ ሐሳብ**

ስልት፤ ራዕያችሁን እና ተልዕኮአችን ከግብ ለማድረስ እሴቶቻችሁን በኑሮ እየገለጣችሁ የምትተገብሯቸው <u>ተለይተው የሚታወቁ</u> ተግባራት ጥርቅም ነው።

የአሰልጣኙ መምሪያ፡- እንዲህ በል "በሞጁል አንድ ስለአምስቱ ቤተክርስቲያን የመትከል ደረጃወች እና ቤተክርስቲያን የመትከል ዙርን ተመልክተናል።" ተሳታፊዎች ከሞጁል አንድ ላይ አምስቱን ቤተክርስቲያን የመትከል ደረጃዎች እና የቤተክርስቲያን ተከላ ዙርን እንዲያነብቡ አድርግ።

እንዲህ በል "ከዚህ ቀጥሎ የሚቀርበው ዝርዝር ከላይ ያነሳናቸውን ሁለቱን በማዋሃድ መሰረታዊ የሆነ የቤተክርስቲያን ተከላ ስልት የሚያዘጋጅ ዝርዝር ነው። የቤትስራችሁ የሚሆነው ከ3-5

የሚሆኑ ለእያንዳንዱ ስልት ምልክት የሚሆን ተለይቶ የሚታወቅ ተግባር መለየትና መወሰን ነው፡፡ ራዕይ እና ተልዕኮ ስታዘጋጁ እንደተጠቀማችሁበት ሁሉ ስልተን ስትነድፉ ከጥናት እና ምርምር ውጤታችሁ ያገኛችሁትን መረጃ የሚያንጸባረቅ መሆን ይገባዋል፡፡"

ከ3-5 ተለይተው የሚታወቁ ተግባራትን በመጻፍ ስልትን ለማዘጋጀት እንዳግብአት ተጠምባቸው፡፡ ስለትህ በጥናትና ምርምር ወቅት የተማርከውን እውነት ማንጸባረቅ ይጠበቅበታል፡፡

## የቤተክርስቲያን ተከላ ስልትን ማደርጀት (45 ደቂቃ)

### ቤተክርስቲያ ተከላ ስልት እቅዱ

I. ጸሎት

1. ______________________
2. ______________________
3. ______________________
4. ______________________
5. ______________________

II. ወንጌል ስርጭት

1. ______________________
2. ______________________
3. ______________________
4. ______________________
5. ______________________

## III. ደቀመዝሙርነት

1. ______________________________
2. ______________________________
3. ______________________________
4. ______________________________
5. ______________________________

## IV. ህብረት (መሰባሰብ)

1. ______________________________
2. ______________________________
3. ______________________________
4. ______________________________
5. ______________________________

## V. የመሪዎች ልማት

1. ______________________________
2. ______________________________
3. ______________________________
4. ______________________________
5. ______________________________

## VI. አምልኮ

1. ______________________________
2. ______________________________
3. ______________________________

4. ________________________________
5. ________________________________

VII. ግቢጋሎት

1. ________________________________
2. ________________________________
3. ________________________________
4. ________________________________
5. ________________________________

VIII. ሡብዛት (ተልዕኮዎች)

1. ________________________________
2. ________________________________
3. ________________________________
4. ________________________________
5. ________________________________

# ለሞጁል 4 የሚሆን የትግበራ እቅድ

**ስቤተክርስቲያን ተከላ የጻፍከውን ስልት አጥራ**

ራዕይ ገላጭ፣ ተልዕኮ ገላጭ እና እሴት ገላጭ አርፈፍተነገሪህን መሰሶ ምልከታንስታደርግ ከመጋቢህ፣ አገልግሎትህን በጸፋ ለማስጀመር ከመርጥከው ቡድን ጋር መሆን ይኖርበታ፡፡

**ቀጣዩ ምንድን ነው?**

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-**

- ለሞጁል አራት የተዘጋጁትን የትግበራ እቅዶች መሰሶ ምልከታ አድርግ (በዚህ ማኑዋል ክፍለትምህርት 5 እና 6ን ተመልከት)፤ ከእነዚህ ጋር የተያያዙ ማንኛቸውም ጥያቂዎች መሰስ ስጥ፡፡
- ከተሳታፊዎች መካከል ፈቃደና የሆኑ ሰዎችን በመምረጥ ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቂዎች በራሳቸው አገላለጽ መልስ እንዲሰጡበት አድርግ፡፡
  1. ረዕይ ገላጭ አርፍተነገር ምንድን ነው? (ክፍለትምህርት 3ን ተመልከት)
  2. ተልዕኮ ገላጭ አርፍተነገር ምንድን ነው? (ክፍለትምህርት 4ን ተመልከት)
  3. እሴት ገላጭ አርፍተነገር ምንድን ነው? (ክፍለትምህርት 5ን ተመልከት)
  4. ቤተክርስቲያን ተከላ ስልት ምንድን ነው? (ክፍለትምህርት 6ን ተመልከት)
- በዚህ ስልጠና የተሳተፉ ሰዎች ስለቤተክርስቲያን ተከላ ያገኙት አስደሳች፣ አበረታች ወይንም አነቃቂ ትምህርት ምንድን ነው?
- እያንዳንዱ ተሳታፊ ለሚመጣው ወር የሚያገለግለውን ግብ ይወስን ዘንድ አበረታታ
- በዝማሬ እና በጸሎት እግዚአብሔርን በመባረክ፤ ከዚያም በዚህ ስልጠና ለተካፈሉ ሰዎች ቡራኬ በመስጠት ክፍለትምህርቱን መዝጋት፡፡

ለሞጁል 4 የሚሆን የትግበራ እቅድ፡- መከታተያ ቅጽ

- ➢ ራዕይ እና ተልዕኮ ገላጭ አርፍተነገሮችን በማደርጀት ለሌሎች አሳይ (ክፍለትምህርት 3 እና 4ን ተመልከት)
- ➢ ዕሴት ገላጭ አርፍተነገር በማደርጀት ለሌሎች አሳይ (ክፍለትምህርት 5ን ተመልከት)
- ➢ የቤተክርስቲያን ተከላ ስልትህን አድርጅ ለሌሎችም አሳይ (ክፍለትምህርት 6ን ተመልከት)
- ➢ ለአንድ ወር የሚሆን የቤተክርስቲያን ተከላ ግብህን አዘጋጅ፡፡

ለአሰልጣኙ የተሰጠ ማስታወሻ፡- ከፍለትምህርት 5 60 ደቂቃ ሙሉ ስለማይወስድ፤ ከዚህ የተረፈህን ጊዜ ለሌላ ጉዳይ ማዋል ትችላለህ ለምሳሌ፡- ከዚህ ቀደም የነበረውን ትምህርት ለመከለስ፣ ለማስተማር፣ በትናንሽ ቡድን ሆኖ ለመጸለይ፣ ተሳታፊዎች ያላቸውን ጥያቄ እና የገጠማቸውን ተግዳሮት ለመፍታት ወይንም ቀደም ብሎ ከዚህ ትምህርት መሰናበት ያለባቸውን ማወቅ ይህን ትርፍ ጊዜ መጠቀም ይቻላል፡፡

| ለዚህ ወር የሚሆን የቤተክርስቲያን ተከላ ግብ | |
|---|---|
| **ግለሰቦች** | |
| የተዋወቅናቸው ሰዎች | እባክዎን በቁጥር ያስቀምጡ |
| ወደጌታ በቅርብ የመጡ | እባክዎን በቁጥር ያስቀምጡ |
| በቅርብ የውሃ ጥምቀት የወሰዱ | እባክዎን በቁጥር ያስቀምጡ |
| በስልጠና ላይ ያሉ መሪዎች | እባክዎን በቁጥር ያስቀምጡ |
| **ትናንሽ ቡድኖች** | |
| አዳዲስ ትናንሽ ቡድኖች | እባክዎን በቁጥር ያስቀምጡ |
| በትናንሽ ቡድኖች ውስጥ የሚሳተፉ አባላት | እባክዎን በቁጥር ያስቀምጡ |
| በጥናት ቡድኖች ውስጥ ያሉ መሪዎች | እባክዎን በቁጥር ያስቀምጡ |